# አብረህ አዝግም

የቀደሙን ሰዎች አነጋገራቸው መሬት ጠብ አይልም ነበር ሲባል የሰማሁት ሁሉ እውነትነቱን በሚገባ አረጋግጫለሁ። እውነትን እንደሚገባን አድርገው በምሳሌ ያስቀምጡልናል። አነጋገራቸው ሳይንስ ነው። ከሁኩም በላይ ደግሞ **ጅል ለጅል አብረህ አዝግም** የሚለው አባባል እርካታ ይሰጠኛል።

የማይነጋ መስሏት በቋቷ ላይ . . . . . .<br>
መልከጥፉን በስም ይደግፉ . . . . .<br>
ከጅብ የማያስጥል ያህያ ባል<br>
ሊበሏት ያሰቧትንን አሞራ ጅግራ ናት ይሏቷል<br>
አህያወን ፈርቶ ዳውላላውን . . . ብዙ ብዙ አባባሎች አሉ።

ከሰላሙ ትግል መስክ ተገፍቶ የተባረረው ኢሕአፓ የትጥቅ አመጹን ሲጀምር የሚከፍለውን መራራ የህይወት መስዋእትነት በሚገባ ተረድቶት ነበር። ለመግደል መሞት እንዳለ ኢሕአፓ በውል ተገንዝቦት ነበር። ከሰላማዊው ትግል እንዲወጣ ከመገፋቱ በፊት ደርግን በተለያዩ የትግል ስልቶች ተጠቅሞ መውጫ መግቢያ አሳጥቶት እንደነበር ራሱ ደርግ ተናግሮታል። ዲሞክራሲያ በፋሺስቱ መንግስቱ ሓይለማሪም ግቢ ውስጥ ተበትኖ ነበርን ማን ያምናል ራሱ መንግስቱ ባይናገረው ኑሮ። ባዲስ አበባም ሆነ በሌሎቹም ክፍለሃገራት በዚያን ወቅት ኢሕአፓ ከሰላሙ ትግል ሌላ መሳሪያ አላነሳም ። የመናገር የመሰብሰብ መብት መጠየቅ መበረታታት ነበረበት እንጂ መወገዝ ባልተገባው ነበር። ኢሕአፓ የደሞዝ ጭማሪ ለሰራተኛው መጠየቁ፡ መሬት ላራሹ መጠየቁ፡ የመናገርና የመሰብሰብ መብት እንዲከበር መጠየቁ ቢያስመሰግነው እንጂ የሚያስገድለው ባልሆነ ነበር። ስለሰላማዊ ትግል መናገር ከኢሕአፓ ወዲይ ላሳር!!!

የሰላሙ ትግል ለሞትና ለሽብር ካጋለጠ ኢሕአፓ ጫካ መግባቱ በከተማም ራስን ከመመከቱ አኳያ መሳሪይ ማንሳቱ ጀግና ያስብለዋል እንጂ ሌላ ምን ሊሆን? ደርግም ጨፈጨው። ወያኔም ጨፈጨፈው። መጥፋት የነበረበት ያኢሕእፓ ሞትን አሸንፎ ዛሬም የአገር ብቸኛ አለኝታ ሆኖ አለ። ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ የሚበጀው የትግል ስልቱ ሁለገብ መሆኑን ገና ከጽንስሱ ያውቀዋል። ትግሉ ሁለገብ ነው – ሰላማዊና የትጥቅ ትግል!! እንዱ ላንደኛው ድጋፉ ነው። የመሳሪያ ትግል ያለ ሰላማዊ ትግል የመሳሪያ ትግሉም ያለ ሰላማዊ ትግሉ መሳካቱ አጠራጣሪ ስለመሆኑ ከኢሕአፓ ወዲያ ላሳር!!!!!

ወያኔዎች የራሳቸው ሕዝብ በተጠራጠራቸው ወቅት ፈጣን ድልን ለመቀዳጀት የቀየሱት ዘዴ በደርግ ውስጥ ሰርጎ መግባት ነበር። ያኔ መቀሌ፡ አዲግራት፡ ሽሬ፡ አክሱም፡አደዋ ... ያለው ወጣት ባብዛኛው ኢሕአፓ ነበር። ወያኔ አባላቱን በደርግ ካድሬነት በማሰማራት ኢህእፓ ናቸው ብሎ የሚጠረጥሩትን ሁሉ ያለ አዘኔታ በቀይ ሽብር ስም አስጨፈጭፋቸው!! በትግራይ ወያኔ የበላቸው ወጣት ቁጥር ወደፊት ለታሪክ ይቀርባል። ዛሬ ወያኔ ስለኢሕእፓ ብዙ መጥፎ ቢያወራ እውነት እውነት ናትና . . ጨለማው መጥራቱ አይቀር!!!

ያን ሁሉ ሰቆቃ የተወጣው ኢሕአፓ ትግሉን ቀጥሎ ባንድ በኩል ደርግን ባንድ በኩል ወያኔን በሌላ በኩል ደግሞ ሻቢያንና ሱዳንን መክቶ የዛሬዋን ኢትዮጵያን አቆይቶልናል። ይህን ማድረጉ ሊያስመሰግነው እንጂ እንዴት ሊያስወቅሰው ይቃጣል? ዛሬ ወያኔ ለሱዳን ያሳለፈውን ኬላ ኢሕእፓ አስከብሮት እኮ ነበር። ዛሬ ሱዳኖች ያን ኬላ ደበደቡት፡ አቃጠሉት ፡ መሬቱን ሰረቁት። ጀግኖቹን አስረው ወደሱዳን እስርቤት ወረወሩአቸው። አገር

አጥፊው ወያነ እንኳን ድንበራችንን ሊጠብቅ ቀርቶ ከሱዳኑ ወታደር ጋር ማበሩን ስናይ **የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ . .** ሆነ ነገሩ!!

ምናልባት ለምን ስለኢሕአፓ ማውራት ተፈለገ ብሎ አንዳንድ የዋሕ ወይም ተንኮለኛ ሊጠይቅ ይችል ይሆናል፡፡ ቢጠየቅም አይከፋም፡፡ ቁምነገሩ ተገቢውን ምላሽ ከመስጠቱ ላይ ነው፡፡ ስላለፉት ሶስት መንግስታት ለማውራት ኢሕአፓን ወደጎን መተው የማይቻል ብቻ ሳይሆን መታሰበም ስለለለበትም ጭምር ነው፡፡ በዚህ እጭር አመታት ኢሕአፓ ለናት ሃገሩ በመቶ ሺዎች ህይወት ገብሯል፡፡ መገበር ብቻ ሳይሆን የውሻ ያህል ክብር እንኳን ሳያገኝ ተጨፍጭፏል፡፡ ኢትዮጵያዊነትን ለመስለብ ኢሕአፓን ማጥፋት ስለመሆኑ ከወያኔ በላይ ያወቀ ማን ሊገኝ?

ማቆየት ሌላ የቆየውን መንከባከብ ደግሞ የተለየ ሌላ፡፡ የኢሕአፓ መዳከም የጎንደር ድንበር ያለማን አለብኝ በሱዳኖች እንዲበዘበዝ ተጋልጧል፡፡ እነዚህ ሱዳኖች ምንኛ ግም ናቸው? የማይነጋ መስሏት ከቆታ ላይ . . . እንድደተባለላት ዶሮ ሱዳንም ነገ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማይነጋ አድርጎ ማሰቡ የማይረባ የዋሆች መሆናቸውን ያሳያል፡፡ በናት ሃገርና በሚስት የለም ዋዛ፡፡ ባንድ ነፃ ናት በተባለች አገር ላይ የውጭ ወራሪ መሬት ሲቀማ፣ ንብረት ሲያቃጥል ዜጋዎቻችንን እስሮ ወደ ሱዳን ሲያግዝ በደስታ የሚመለከት መንግስት መኖሩ ማበሳጨት ብቻ ሳይሆን እንኳን የጎንደርን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላ የኢትዮጵያን ህዝብ ላመጽ ማነሳሳት ያንስበታል፡፡ በርግጥ ያ ቆራጡ የኢሕአፓ ሰራዊት ከምድረ ጎንደር መጉደሉ ዛሬ ከመቸውም በበለጠ ያመጽ ትግል ጥሪ ስለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

ኢሕአፓ ካፈጣጠሩ ጀምሮ ጠላትን ለማንበርከከ ያለው የትግል ዘዴ አንድና አንድ ብቻ ነው ብሎ አልሰበከ፡፡ ህዝባችንንና ሃገራችንን ነጻ ሊያወጣ የሚያስችል ማንኛውንም የትግል ስልት እጠቀማለሁ ነው ያለው – **ሁለገብ የትግል** ስልት!!! ይህ የጸና አቋሙ ነው፡፡ ትናንት ጠመንጃ ነካሽ ያሉት ዛሬ ያመጽ ትግል አንድ ሁለት ሊያስተምሩን ካሜሪካን ተራራ ላይና ከለንደን ከተማ የቱልቱላ ሞገዳቸውን ሲያወናጨፉ ማስተዋል ከጀመርን ሰንብተናል፡፡ ድራማው በውስጡ በርካታ ጉዳጉዶችን ማጎሩ ለብዙዎቻችን ግልጽ ላይሆን ይችላል፡፡ ላንዳንዶቻችንም ሃሜት የሚመስል ዜና ሁኖም ታይቶን ሊሆን ይችላል፡፡ የተነሳው አውሎ ነፋስ ሲሰክን ጉዳጉዶቹን እንደምንለይ አያጠራጥርም፡፡

መቸም ሁለገብ የምትለዋ የትግል ስልት ለብዙዎቹ አስመሳይ ፖለቲከኞች የማትመች የውስጥ እግር እሳት ነበረች፡፡ ያለሰላማዊ ትግሉ በስተቀር ሞቼ እገኛለሁ እንጂ አመጹማ አገር ያጠፋል እንዳላሉን ዛሬ ባለወኔውች ሁነው ተነሳ ላመጽ ሲሉን እሰየው ብለን ከመጋለባችን በፊት ልብ ልንለው የሚገባን ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ **ልብ ያለው ልብ ይበል**፡፡ የሰላሙን ትግል እንድንገፋና የልመና ደብዳቤ ላቶ መለስ እንድንጽፍ ኢሕአፓን ያመሱት ልዝብ ሰይጣኖች ዛሬ ባንጃነት ከድርርጅቱ ራሳቸውን አግለው በድርጅቱ ስምና ልሳን የህዝቡ ትግል ጥራት እንዲያጣ ሲያወናብዱት ይታያሉ፡፡ እውነት ስለሌላቸውና ደካማ ስለሆኑ ነው እንጂ ጎበዝማ ቢሆኑ ኑረው የራሳቸውን ስም ሰይመው የራሳቸውን ልሳን ቀርጽው የራስቸውን የፖለቲካ ፕሮግራም ዘርግተው በታገሉና መዥገር መሆናቸውን በተውት ነበር፡፡ **መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ** ካልሆነ በስተቀር፡፡

ሌላው ድራማ በቅንጅቱ የታየው የተዘበራረቅ ያንጃነት ድራማ ነው፡፡ የነ ነጋ፣ ጵጌ፣ መዋ አንጃ አመራሩን የሰጠው ለብርቱኳን ይመስል ነበር፡፡ እርሷ ደግሞ ሃገር ቤት የራስዋን ግሩፕ የያዘች ይመስላል፡፡ በነጋ የሚመራ የሚመስለው ክንፍ በሰላሙ ትግል ላይ ተሳልቆ ወደ ጠምንጃው ትግል ፊቱን እንዳዞረ ይስተዋላል፡፡ ብራሾ ነጋ ድንቄም ዶክተር፡፡

**ጀርባዬን እከክልኝ ጀርባህን ልከከልህ** ሆነና የኢሕአፓውና የቅንጅቱ አንጃ ውስጥ ውስጡን ሲስማሙ ከርመዋል፡፡ ሃሜት ይመስላል ግና ሀቅ ነው፡፡ **እውነትና ንጋት እየዋለ ይጠራል**፡፡ ነጋ ስለ ትጥቅ ጥግሉ ከቲዎሪ ባሻገ ብዙ ባያውቅም በዚህ እድሜ ለኢሕአፓ ይበል መርሻን

አግኝቷል። የመርሻው አንጃ ብር የሚያጥረውና ደጋፊም በጣት የሚቆጠር በመሆኑ ይህን በነጋው ጎራ ያካክሰዋልና ጥምራቸው ሚዛናዊ ይመስላል። የዘር ልጎምም አሳስቧቸዋል የሚል ሃሜት መኖሩን ባልደግፈውም መወራቱ ግን ትክክል ነው። ዋነኛው ችግራቸው ግን ስለ ሰላማዊ ትግሉ ሲያስተምሩት የነበረውን ሕዝብ እንዴት አድርገው ነው ስለ ትጥቅ ትግል ሊያስተምሩት የሚሞክሩት? ለመሆኑ ህዝቡን ሂዱና ጠብመንጃ ያዙ ብለው ሊያዙት ነው ወይስ እኛ ምሳሌ እንሆንሃለን ተከተሉን ሊሉት ነው? ሁለቱም መንገድ እንደማያዋጣቸው ያውቁታል። ምናልባት ሊሉት የሚችሉት ሰራዊት አለን እናንተ ግን በገንዘቡ ተባበሩን ነው። ለማስረጃ የድቡብ ሱዳን ወይም የዩጋንዳ አማጽያንን ፎቶ ሊደረድሩልን ይችላሉ። አለያም የኡጋዴንን ወይም የኦሮሞውን ሰራዊት ፎቶ ሊያቀርቡልን ይችላሉ። ፎቶውን ብቻ ሳይሆን ከነነብሱ የሻቢያንንም ሰራዊት በምድረ ኢትዮጵያ ላይ ሊያሳዩንም ይችላሉ። **AFD**!!!! ይህቺ ናት ትግል። **ጆል ለጆል አብረህ አዝግም** አይነት።

የትግል ስልት በፍላጎት ወይም በምኞት ወይም በቅዠት የሚቀረጽ ቀምር አይደልም። ከተጨባጨና ተጨባጭ ካልሆነው ሁኔታዎች ይፈልቃል። የኑሮ ውድነቱ፣ ስራ ማጣቱ፣ ፍትህ መጓደሉ፣ ወዘተ የመሳሰሉት ለነ ነጋ የማያስጭንቁ ችግሮች ህዝቡን ሲያውኩት ነው። ***መራብ ለነ ነጋ ቁርስ መሳቱ ሊሆን ይችላል። ስራ ማጣት ለነዚህኞቹ የስድስት ቁጥር የደሞዝ ብዛት አለማግኘት ሊሆን ይችላል። ወይም ለተራ የማጭበርበሪያ ፖለቲካቸው ከሚጋልቡት ምስኪን በውጭ ኗሪው ህዝብ የሚጠበቀውን መዋጮ አለማግኘት ሊሆን ይችላል።*** እነዚህ ጉዶችና ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አካሄዳቸው ለየቅሉ ነው – **ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲይ**!!!

***ነገር ቢበዛ ባህያ አይጫንም ነውና*** ባጭሩ በቅርቡ ከየድርጅቶች ተንገዋለው የፈረጠጡ እንጃዎች እንድ ግንባር ፈጥረናል ቢሉን መደነቅ የለብንም። ብሎም ግንባሩ የትጥቅ ትግል ጀመርኩ ማለቱም አይቀርም። ለጦሩ ገንዘብ ለማሰባሰብ በየአካባቢው እንቀሳቀሳለን ብለው የጉብኝት ፕሮግራም ማውጣቸውም አይቀርም።

ትግሉ መልኩን ቀይሮ ካጓጉል ሜዳ መግባቱን በቁጭት እናስተውለዋለን። ትግሉ ከወያኔ ጋር መሆኑ ቀርቶ ትግሉ እርሰ በርስ – ቅንጅት ከህብረት . . . ቅንጅት ከራሱ ጋር . . . ኢሕአፓ ካንጃው . . . ህብረቱ ያጎረሰ እጁን መንከስ የታየበት . . .

ዛሬ የሚታየው ትግል ግራ ማጋባቱ ብቻ ሳይሆን መሰሪም ነው። ያልተሞከረ ይመስል እንደ እዲስ ግኝት የትጥቅ ትግል ስባኪዎች ማቆጥቆጥ ጀምረዋል። ግምቴ ስህተት ቢሆን አመኛለሁ ግን ያንጃዎች የትጥቅ ትግል እውነት ከሆነ ጦራቸው ኢላማው በወያነ ላይ ሳይሆን በኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆችና ኢሕአፓ ላይ እንደሚሆን ሳንጻፍታም መጠራጠር የለብንም።

**እና ምን መደረግ አለበት?**

1. *የአንጃዎችን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ በመከታተል ማጋለጥና ከህዝቡ ጎራ መነጠል*
2. *ትግላችን ከወያኔና ከልዝብ ሰይጣኖቹ እንድጃዎችትም ጋር መሆኑን አለመርሳት*
3. *በህዝቡ የተቀጣጠለውን ያምጽ ትግል ድርጅታዎ አመራር መስጠት*
4. *የመርሻናን የብርሃኑን የቅዠት የትጥቅ ትግል ምኞት ካሁኑ ማክሸፍ*
5. *መጀመሪያ የመቀምጫዬን ዝጀሮዋ እንዳለችው . . . የሁላችንም ትኩረት መሆን ያለበት ሃገርን ማዳን ነው። የጎንደር ድንበራችን መወረር አጣዳፊ ጥሪ መሆኑን ተገንዝቦ ተገቢ ምላሽ ለመስጠት መዘጋጀት*

*ይዘገያል እንጂ ድል የማይቀር ነው*!!!!!